ማርች 30ቀን 2020ዓ.ም.

***ይህ ማገናኛ መረብ መልእክቱን በአማርኛ ቋንቋ ለማግኘት ያገለግላል።***

በዚህ የተለየ ጊዜ የተማሪዎችን ትምህርት ቀጣይነት ለመደገፍ FCPS የርቀት ትምህርት ዕቅዱ አንድ አካል የሆነውን የትምህርት ጥቅል/እሽግ እያደለ ይገኛል። እነዚህ ጥቅሎች/እሽጎች የተሻሻለ ሥርዓተ-ትምህርት ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጁ ናቸው። በየሳምንቱ ጥቅሎቹ/እሽጎቹ ሂሳብ፣ ንባብ ፣ እንቅስቃሴ እና የሳይንስ/የማህበራዊ ጥናቶች ከሌሎች አስፈላጊ ስራዎች እና ቤተሰቦችን ለማገዝ የሚረዱ የቤት ውስጥ አስፈላጊ ክህሎቶችን ያካትታሉ። ሁሉም እንቅስቃሴዎች እንዴት መገናኘት እንደሚችሉ እንዲማሩ ለመርዳት በእንቅስቃሴዎቹ ውስጥ የተካተቱ የግንኙነቶች ክህሎቶች አሉ።

በሚቀጥሉት በርካታ ሳምንታት ውስጥ ቤተሰቦች የትምህርት ጥቅሎችን/እሽጎችን ወደ ቤታቸው እንሚላኩ እና በጥቁር ሰሌዳ ላይ እንደሚለጠፉ ይጠብቁ፡፡ እባክዎን የሚከተሉትን ታሳቢ በማድረግ መረጃዎችን ይጠቀሙ፡-

- በተሻሻለው ሥርዓተ-ትምህርት ለተመዘገቡ ከK – 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ጥቅሎች/እሽጎች ይላካሉ።
- ከፀደይ የእረፍት ጊዜ (ከኤፕሪል 6-10) በስተቀር በየሳምንቱ በፖስታ ይላካሉ።
- ጥቅሎቹ/እሽጎቹ በሳምንቱ ውስጥ በቤተሰቦች እና ተማሪዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የታሰቡ ናቸው።
- ቤተሰቦች ከተማሪዎች ጋር በትምህርቱ እንዲካፈሉ ይበረታታሉ፡-
    - እንደአስፈላጊነቱ የእንቅስቃሴ አቅጣጫዎችን ይገምግሙ።
    - ጥያቄዎችን ይጠይቁ።
    - እንቅስቃሴዎችን አንድ ላይ ለማጠናቀቅ ያስቡበት።
    - ልጅዎ እንቅስቃሴዎችን ለእርስዎ/ለሌሎች ሲያካፍል ያዳምጡ።
- ጥቅሎች/እሽጎች እንደ አማራጭ ናቸው። የውጤት ደረጃ አይሰጥባቸውም።

በጥቅሉ/እሽጉ ውስጥ ስላለው እንቅስቃሴ ጥያቄዎች ካለዎት እባክዎን የልጅዎን መምህር ያነጋግሩ።